ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ጥቅምት 2001 ዓ.ም. **የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች** ቁጥር 17

# የግብርና ኤክስቴንሺን በኢትዮጵያ ፦ ታሪካዊ ሂደቱ፣ ተጓዳኝ ፖሊሲዎችና መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች

♦ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❋ ❋ ❋

♦ የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❋ ❋ ❋

♦ በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❋ ❋ ❋

♦ በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❋ ❋ ❋

♦ በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## 1. መግቢያ

በቅርቡ የወጣ የመንግስት ሪፖርት እንደሚያመለክተው 5 ሚሊዮን የሚሆኑ የሀገሪቱ ዜጐች በተደጋጋሚ በየዓመቱ፣ከዛ የሚበልጡ ሌሎች ዜጐች ደግሞ አልፎ አልፎ በሚያጋጥም የምግብ እጥረት ችግር ይጠቃሉ። በመሆኑም ይህን ችግር ማቃለል የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር ሆኗል። የግብርና እድገት የምግብ ዋስትና ማጣትን ለማቃለል ይረዳል። የግብርና ኤክስቴንሽን ደግሞ የግብርና ልማትን ለማምጣትና የተፈጠሮ ሀብትን ለመጠበቅ ቁልፍ ሚና አለው። የኤክስቴንሽን ንድፈ-ሀሳብ ተለዋዋጭ በመሆኑ በአለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ አንድ አጠቃላይ ትርጉም ለመስጠት አልተቻለም። ጠቅለል ባለ መልኩ ኤክስቴንሽን መንግስት በህብረተሰቡ ዘንድ ተፈላጊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ለውጦች ለማምጣት የሚጠቀምበት ህጋዊ የሆነ የፖሊሲ መሣሪያ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይቻላል። በተለይም የግብርና ኤክስቴንሽን ዋና ዋና ተግባራቱ የሚከተሉት ናቸው፤

- ለግብርና ምርት ዕድገትና ግብይት መሳካት የሚረዱ መረጃዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣
- የገበሬዎችን አደረጃጀት ጥንካሬ በማገዝ ያሉባቸውን ችግሮች በመለየትና አቅማቸውን በማስተባበር የጋራ ራዕይና ግብ ይዘው በአንድነት እንዲሰሩ ማገዝ፣
- የገበሬዎችን የሰው ኃይል፣ የተፈጥሮ ሃብት፣ የካፒታልና የቴክኒክ አቅም በማሳደግና የማስተዳደር ችሎታቸውን በማዳበር የመደራደርና የተሻለ ዋጋ እንዲሁም መረጃና ድጋፍ የማግኘት አቅማቸውን ማሳደግ።

ይሁን እንጂ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ግቦች እንደየ ሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታና የልማት አቅጣጫ የሚወሰኑ ሲሆን የግብርና ኤክስቴንሽን ዓላማና ተግባራትም በሀገሪቱ ፖሊሲዎች አኳያ የሚቃኙ ናቸው። ይህ ጥናት የግብርና ኤክስቴንሽን በኢትዮጵያ የነበረውን ታሪካዊ ሒደት፤አሁን ያለበትን ሁኔታና ኤክስቴንሽኑን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን በመቃኘት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለመለየት ይረዳ ዘንድ በማህበራዊ ጥናት መድረክ አማካኝነት የተከናወነ ነው። ጥናቱም በሰነዶች ቅኝት ላይ የተመሰረተ ነው።

## 2. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 2.1 የግብርና ኤክስቴንሽን ታሪክ፣ ትኩረትና ወሰን

ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ ግብርና የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ያለው ቢሆንም ግብርናውን በተቀናጀ መልኩ ለማሻሻል ጥረት መደረግ የተጀመረው ግን በቅርብ ነው።

የግብርና ኤክስቴንሽን ሲባል የሚሰራቸውን ሥራዎች ብቻ ሳይሆን ግልጋሎቱን በተቀናበረ መልኩ ለመስጠት የተደራጀበትን አደረጃጀትም ይጨምራል። ይህ አደረጃጀት በመንግስት፣ የመንግስት ባልሆኑ ድርጅቶችና በግል ተቋማት የሚሰጥ የማስተማር፣ የማስተባበርና የማማከር ስራዎችንም ያጠቃልላል። ትክክለኛ የኤክስቴንሽን አደረጃጀት የሚባለው ብዙ ገበሬዎችን በፍላጐታቸው ላይ ተመስርቶ በዝቅተኛ ወጪ ግልጋሎት ማቅረብ የሚችል ነው። በመሆኑም ኤክስቴንሽን በቀጥታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው መልዕክት ከማስተላለፍ ወደ አሳታፊና የጋራ የመማሪያ መድረክ ስርዓት እየተቀየረ ነው። በአለም ውስጥ ያሉ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግና በወቅቱ የግብርና ኤክስቴንሽን የገጠሙትን መሰናክሎች ታሳቢ በማድረግ ሚዛናዊ የሆነ፣ ትክክለኛና በቀላል ወጪ ግልጋሎት ለማዳረስ የሚያስችል የአደረጃጀትና አተገባበር ተሞክሮዎች ያሉ ሲሆን እነኚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ መጥተዋል። በሀገራችን ግን እስካሁን የተከናወኑ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች የኤክስቴንሽን ሥርዓቱን ጠቃሚነትና ወጪ ቆጣቢነት ለማሻሻል ብለውና ከዚህ በፊት በተከናወኑት ተሞክሮ ላይ ተመስርተው የተነደፉ ለመሆናቸው ብዙ ማስረጃዎች የሉም።

በ1890 አካባቢ ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎች፣ አዳዲስ የዛፍ ዝርያዎች (ለምሳሌ የጐማ ዛፍ፣ የባህር ዛፍ ...ወዘተ) እና የተሻሻሉ የመስኖ ስርዓት ለማስተዋወቅ ጥረት ተጀመረ። የተቀናጀ መንግስታዊ ድጋፍ በመስጠት ግብርናን ለማሳደግ ጥረት የተጀመረው ግን በ1901 ዓ.ም

በምኒልክ መንግስት የእርሻ መ/ቤት የተባለው ከተቋቋመ በኋላ ነበር። ይህ መ/ቤት የተሰጠው ኃላፊነት ገበሬዎችን በሰብል ምርትና በእንስሳት እርባታ ማማከር፣ ደንና ዱር አራዊትን መጠበቅ፣ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት መስጠት እና አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን መሰብሰብ ነበር። በ5 ዓመቱ የጣልያን ወረራ ወቅት የተጀመረው የግብርና ልማት ስራ ተቋረጠ።

በ1938 የግብርና ሚ/ር ራሱን ችሎ ተቋቋመ። ሚኒስቴሩ ሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎች በመክፈት ከውጪ የመጡ የከብት፣ የበግና የዶሮ ዝርያዎችን በማርባት ለሀገሪቱ ያላቸውን ተስማሚነት መፈተሽ ጀመረ። ክትባት በማምረት ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ በሽታዎችን ለመቆጣጠርም ጥረት ተጀመረ። በ1945 ሚኒስቴሩ የአለማያ እርሻ ኮሌጅን በመክፈት በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄደውን የእርሻ ትምህርት፣ ምርምርና ኤክስቴንሽንን እንዲያስተባብር ማድረግ ጀመረ። የኮሌጁ የኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎች አካባቢ ያሉትን ገበሬዎች በማስተማር፣ የአዋቂዎች ትምህርታዊ ስብሰባዎች በማካሄድና የወጣቶች የግብርና ክበቦች በማቋቋም ብዙ ስራ ሠርተዋል። የግብርና ሚኒስቴር ሀገራዊ የኢክስቴንሽን ማስተባበር ኃላፊነቱን በ1955 ከአለማያ ኮሌጅ በመውሰድ ኮሌጁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥር እንዲሆን ተደረገ። ይህን ወቅት ብዙዎች የግብርና ትምህርት፣ ምርምርና ኤክስቴንሽን የተለያዩበት የታሪክ ወቅት አድርገው ይወስዱታል።

የግብርና ሚ/ር የግብርና ኤክስቴንሽንን ስራ የሚመራ መምሪያ አቋቁሞ በየክፍለ ሀገሮች የኤክስቴንሽን ሱፐርቫይዘሮች ላከ። በየአውራጃውና ወረዳዎችም ሠራተኞች ተመደቡ። እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ ድረስም የማዳበሪያ ሰርቶ ማሳያ ስራዎች፣ሁሉን አቀፍ ፓኬጅ በኋላም አነስተኛ ፓኬጅ ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ዘመናዊ ግብርናን ለማስተዋወቅ ተሞክሯል።

ይሁን አንጂ በዘውዳዊው ስርዓት ወቅት የግብርና ኤክስቴንሽን ግልጋሎት የደረሰበት አካባቢ ውሱን ነበር። ተገልጋዮችም በአብዛኛው ባለመሬቶች፣ ዘመናዊ ገበሬዎችና የፕሮጀክት ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ያሉ ጥቂት አርሶ አደሮች ብቻ ነበሩ። የሀገሪቱ የልማት ፖሊሲ የግብርና ዘርፉን ያገለለ በመሆኑ ዘርፉ የተመደበለት በጀት ከ2% ያልበለጠ ነበር። የምርምርና የኤክስቴንሽን ግንኙነትና መደጋገፍም የላላና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሌሎቹ ግልጋሎቶች (ከግብአት አቅርቦት፣ ከብድርና ከገበያ) ጋር ያለው መደጋገፍ የተጠበቀውን ያህል አልነበረም። በተለይም የኤክስቴንሽን ግልጋሎት ለብዙሃኑ ገበሬዎች ሊሰጠው ይችል የነበረውን ግልጋሎት የመሬት ስሪቱ አስሮ ይዞት ቆይቷል፡

የኃይለ ሥላሴን መንግስት በመስከረም 1967 በመጣል ደርግ ሥልጣን ላይ ወጥቶ የመሬት ላራሹን አዋጅ አወጣ። ኢፒድ የተባለው የግብርና ሚኒስቴር መምሪያ የመሬት ላራሹን አዋጅ ለመተግበር ታዘዘ። በ1969 የኤክስቴንሽን ሥራዎችን ለማቀላጠፍ እንዲያስችለው የግብርና ሚኒስቴር የሰብል፣ የእንስሳት፣ የደን፣ እንዲሁም የአፈርና የውሃ ጥበቃ መምሪያዎችን በስሩ አደራጀ። አንዳንድ ጥናቶች ይህ ውሳኔ የኤክስቴንሽን ሥራ አስተዳደርን ማስተባበርንና ቁጥጥርን በሰፊው እንደጐዳ ይገልፃሉ። በ1971 ገበሬዎችን በማህበራት የማደራጀት መመሪያ ወጣ። ይህም በሞዴል ገበሬዎች ላይ ተመስርቶ የነበረው የኤክስቴንሽን ግልጋሎት ስርዓት ወደ ማህበራት እንዲዞር አደረገ። የአነስተኛ ፖኬጆች ሥራም ከ1974 እስከ 1981 ቀጠለ።

የደርግ ሥርዓት የጨሰኛና የባላባትን ግንኙነት አፍርሶ የገበሬዎችን የመሬት ይዞታ ዋስትና ለማጠናከር ሞከረ። የገበሬዎችን ማህበራት በማቋቋም የገበሬዎችን ድርጅታዊ አቅም ለማሳደግ ጣረ። ነገር ግን የግብርና ምርምር አቅምንም ለማሳደግም ሞከረ። ነገር ግን የድርቅ መደጋገምና የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጠበቀ የገበያ ቁጥጥር፣ የገበሬዎች በሰፈራና በመንደር ምስረታ መንገላታት፣ ወጣት ገበሬዎችን ለውትድርና መመልመል የግብርና ዕድገቱን አቀጨጨው። በተለይም ገበሬው ምርቱን በተወሰነ ዋጋ ለገበያ እንዲያቀርብ የገበሬ ማህበራትንና የአገልግሎት ህብረት ሥራ ማህበራትን ለአስገዳጅነት መጠቀሚያ ማድረጉ ምርትንና ምርታማነትን ከመቀነሱም በላይ ገበሬው በማህበራት ላይ እምነት እንዲያጣ አድርጎታል። አነስተኛ ገበሬዎችን ከመርዳት ይልቅ መንግስት ድጋፉን በአብዛኛው ለማህበራትና ለመንግስት እርሻ ልማቶች በመስጠቱ የግብርና ኤክስቴንሽን ለልማት ሊኖረው ይችል የነበረውን አስተዋጽኦ በእጅጉ ጐድቶታል።

የደርግን መንግስት አስወግዶ ሥልጣን የያዘው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡን በፌደራል መንግስት ስርዓት እንዲደራጅ እና አገልግሎቱም ቀልጣፋ እንዲሆን እንዲገመገም አደረገ። መንግስት የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን እንዲገመግም ያቋቋመው የጥናት ቡድን አገልግሎቱ ያሉበትን የአደረጃጀት ችግሮች፤ ሠራተኞቹ ያለባቸውን የአመለካከት ችግሮች፤ እና ሥርዓቱ ያሉበትን አስተዳደራዊ ማነቆዎች በዝርዝር ለይቶ አቀረበ። ገበሬዎችን በማደራጀት ዙሪያ ብዙ አለመስራቱን፣ ገበሬዎች በቴክኖሎጂ ብዜትና ስርፀት ውስጥ ተሳታፊ አለመደረጋቸውን በምርምሩና በኤክስቴንሽን እንዲሁም በኤክስቴንሽን በብድርና በገበያ አካላት መካከል ያለው ግንኙነት የላላ መሆኑን፣ የማስተባበርና የማቀናጀት ችግር በስፋት መታየቱና የገበሬዎች ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ በዝርዝር ቀረበ። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ይረዳ ዘንድ ሀገራዊ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም በፌደራል መንግስት ደረጃ ተቀርጾ ክልሎች ግን የራሳቸውን ዕቅድ እንዲያወጡ፣ እንዲፈጽሙና እንዲገመግመ ሙሉ ነፃነት ተሰጣቸው። በዚሁ ጊዜም ሳሳካዋ ግሎባል 2000 በምግብ እህሎች ላይ አሉ የተባሉ ቴክኖሎጂዎችን በማሰባሰብ ለገበሬዎቹ የማስተዋወቅ ስራ ጀመረ። የዚህን ፕሮግራም ስኬት መሠረት በማድረግ አዲሱ አሳታፊ የሠርቶ ማሳያና ማሰልጠኛ የኤክስቴንሽን ሥርዓት ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ተግባራዊ መሆን ጀመረ። የምግብ፣ የኢንዱስትሪና ለወጭ ገበያ የሚውሉ ሰብሎች ላይ በማተኮር አቅርቦት ማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት፣ እና የገበሬዎችን አቅም መገንባት ዋና ዋና ዓላማዎቹ ናቸው። ለየአካባቢዎች ተስማሚ የሆኑ ፓኬጆችም እየተዘጋጁ በመሰራጨት ላይ ናቸው። የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ቁጥርና የትምህርት ደረጃም በእጅጉ ጨምሯል።

የዚህ የኤክስቴንሽን ሥርዓት ሽፋን በጣም የሰፋ እንደነበረና ከአራት ሚሊዮን በላይ ገበሬዎች ተጠቃሚ እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ። የገበሬዎች ምርትም በእጅጉ ያደገ መሆኑ ተመልክቷል። ነገር ግን ጥናቶች እንዳሳዩት በኤክስቴንሽን ግልጋሎቱ ላይ ገበሬዎች ከማቀድ እስከ ማከናወን ድረስ ብዙም ተሳታፊ አልነበሩም። የብድር አገልግሎትም እንደተሻሻለ ታውቋል። ሆኖም ግን ሀገሪቱ የኤክስቴንሽን ፖሊሲ የሌላት በመሆኑ የኤክስቴንሽን ምንነትና ተግባራት፣ በዚሁ ተግባር የሚሰማሩ አካላት ኃላፊነትና ድርሻም በዝርዝር አለመቀመጡ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ይህም በመሆኑ የተለያዩ አካላት ለኤክስቴንሽን የተለያየ አተረጓጐም በመስጠት የሚመስላቸውን በመስራት ላይ ይገኛሉ። ይህን ፖሊሲ በማውጣት ሥራውን የተቀላጠፈ ማድረግና የስራ ተሳታፊ አካላት ተደጋጋፊነትን በማረጋገጥ ለረዥም ጊዜ የግብርና ኤክስቴንሽን የገጠመውን ችግር ማስወገድ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ ነው።

## 2.2 የግብርና ኤክስቴንሺን ላይ እንደምታ ያሳቸው ስትራቴጅዎችና ህጋዊ ሰነዶች

የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት ወደስልጣን ከመጣበት ከ1983 ጀምሮ የገጠሩን ልማት ለማፋጠን ከሚረዱ በርካታ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች መካከል:-

- የስነ-ህዝብ ፖሊሲ፣
- የግብርና-መር የኢንዱስትራ ልማት ስትራቴጂ፣
- ህገ መንግስቱ፣
- የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ፣
- የአካባቢ ጥበቃ ስትራቴጂ፣
- የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣
- የግብርና ገበያ ስትራቴጅ እና
- የድህነት ማስወገጃ እቅድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በተለይም የወቅቱ የመንግስት የ5 ዓመት የልማት እቅድ የግብርና ኤክስቴንሽን ሊፈፅማቸው የሚገቡ ተግባራትን ዘርዝሯል:: የመንግስት ስትራቴጂዎችና ህጋዊ ሰነዶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገጠር ልማቱ ዘለቄታዊ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ:: የገጠር ልማት ለማምጣት የግብርና ማደግ ወሳኝ እንደሆነ ተጠቁሟል:: የኤክስቴንሽን ስርዓቱም የሰው ኃይልን ለመገንባት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: ይህን ለማድረግም በገበሬዎች ፍላጐት ላይ የተመሠረተ መሆን ያለበት ሲሆን የግብርናን ምርታማነትና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃንም ማገዝ ይኖርበታል::

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በቅርቡ የተደረገ ጥናት አሳታፊ የተባለው የኤክስቴንሽን ሥርዓት ብዙም አሳታፊ እንዳልነበረ፣ በተለይም ለሴቶች ያደረገው ትኩረትና ድጋፍም አጥጋቢ እንዳልነበር፣ ትኩረቱም የተሻለ የማምረት ዕድል ባላቸው ወረዳዎች ላይ እንደነበረ፣ ከሰብል እህሎች ውጪ በሌሎች የግብርናው ዘርፈ ግን ብዙም ሥራ እንዳልተሰራ፣ በተለይም ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ሥራ የዋለው የስራ መጠን እጅግ አናሳ እንደነበር ጥናቱ ይጠቁማል:: በመሆኑም ኤክስቴንሽን ለገበሬው የሚሰጠውን ግልጋሎት ማጠናከር እንዳለበት ተጠቁሟል:: ኤክስቴንሽን ለተለያዩ ሥነ-ምህዳራዊና የተለያየ የኢኮኖሚ አቅም ላላቸው ገበሬዎች ተስማሚ የሆነ ሥራ በመስራት ጠቃሚነቱን ይበልጥ ማሳደግ ይኖርበታል:: ከመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የሚሄድ ሥራ ማቀድና መስራትም ይጠበቅበታል:: ይህን ለማድረግ የኤክስቴንሽን ዘርፍ ያሉበትንና እክሎች ማየትና እነዚህን ለመወጣትም መንቀሳቀስ ያሻል::

## 2.3 የግብርና ኤክስቴንሺንን በተመለከተ መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች

የግብርና ኤክስቴንሽንን ፍሬያማነት የሚገቱ እክሎች በአራት ይከፈላሉ:: እነሱም የተጠቃሚዎች ሁኔታ፣ መዋቅራዊ ችግሮች፣ ቴክኒካዊ እክሎች እና ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ናቸው:: ከዚህ በታች ቴክኒካዊና በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን::

የኢትዮጵያን የግብርና ኤክስቴንሽን ሥራ ለማበረታታት የሚከተሉትን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ማየትና መፍትሄ መፈለግ ይረዳል::

- የኤክስቴንሽን ግልጋሎትን በማስፋትና የሥራውን ጥልቀት በመወሰን ዙሪያ ጥንቃቄ ያሻል:: የኤክስቴንሽን ግልጋሎትን ማስፋት በስራው ጥልቀትና ጥራት ላይ ተፅዕኖ አለው:: እንደኛ ባሉ ብዙ ገበሬዎች ባሉበት ሃገር የግልጋሎቱን አድማስ በማስፋት ለሁሉም ለማዳረስ የሚደረግ ጥረት ፍትሃዊ ሆኖ ይታያል:: ነገር ግን ግልጋሎት በሰፋ ቁጥር ብዙ የሰው ኃይልና ግብአት መጠየቁ እነዚህንም በትክክል ማስተዳደርና ማስተባበር ከባድ ይሆናል:: በመሆኑም ክትትሉና ቁጥጥሩ የላላ ይሆናል:: ከስፋት ጋር የሚመጡ ችግሮችን ለመቅረፍ ገበሬዎችን በሚገባ በማሳተፍ የኤክስቴንሽን ግልጋሎቱን ፋይዳ ማሳደግ፣ ለገበሬዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብና እንደየሁኔታው ወጪን መጋራትም እንደ ጥሩ ርምጃዎች ተደርገው ይቀርባሉ::
- የገበሬዎችንና የግብርናውን ዘርፍ ችግሮች በትክክል መረዳት የግድ ነው::
- የኤክስቴንሽን ትኩረት እስካሁን ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ ላይ እንጂ የገበሬዎችን ችግር የመፍታት አቅም በማዳበር ላይ አልነበረም:: በመሆኑም የገበሬዎችን ክህሎት ማዳበር በጋራ በመደራጀት እንዲሰሩ ማድረግ ራሳቸውን እንዲያበለፅጉ ይረዳል::
- ከምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችን አዋጪነት እንደየአካባቢው ሁኔታ ማጣራትም የኤክስቴንሽን የራሱ ሥራ መሆን አለበት::
- የታሳታፊ ቤተሰቦች አመራረጥ ላይ ኤክስቴንሽን ድሃና ሴቶችን ወደ ጐን በመተው የተሻለ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ጋር በብዛት ሲሠራ ቆይቷል:: በተጨማሪም በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ትኩረቱ ከመንገድ ብዙ ያልራቁ አካባቢዎች ላይ ነበር::
- የመርሐ ግብሩ ስኬት መለኪያዎች ሽፋን ላይ ያተኮሩ ሲሆን ይበልጥ የተሻለ የሚሆነው ግን ውጤት ላይ የተመሠረተ ቢሆን ነበር:: ለምሳሌ ምን ያህል ገበሬዎች የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ታሳታፊ ሆኑ ከሚለው ምን ያህሉ ምርታቸውና ገቢያቸው ጨመረ፣ በምንስ ያህል ቢል የሚሻል ይሆናል::
- የምርምርና የትምህርት ግንኙነት ውጤታማነት ከግብርና ኤክስቴንሽን ውጤታማነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን ምርምሩና ትምህርቱ አነስተኛ ገበሬዎችን መሠረት ያደረገ ሥራ በስፋት እየሠሩ አይደለም:: በመሆኑም ከስራው የሚጠቀሙት ዘመናዊ ገበሬዎች ብቻ ናቸው::
- የግብርና ምርምር፣ የግብአት አቅርቦት፣ የብድርና የገበያ ስርዓቱ ከኤክስቴንሽን ግልጋሎቱ ጋር ያላቸው ትስስርና መደጋገፍ እንዲናበብ ቢደረግ ለግብርና እድገት ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችላል::
- የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ትምህርት በተገቢ መልኩ በግብርና ሙያ፣ በአስተዳደርና አመራር፣ እንዲሁም በመገናኛ ክህሎት (ኮሙኒኬሽን) ዙሪያ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል::

የኤክስቴንሽን ግልጋሎቱን ጠቃሚነት ለማሻሻል ሊተኮርባቸው የሚገቡ ፖሊሲ- ነክ ጉዳዮች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው::

- የግብርና ኤክስቴንሽንን ምንነት በሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ መወሰንና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ድርሻም ግልጽ ማድረግ የሚሻል ይሆናል:: የኤክስቴንሽን ፖሊሲ

አለመኖር የግብርና ኤክስቴንሽን ምንነትና ተግባራት ላይ ብዥታና አለመግባባትን ይፈጥራል። የግብርና ፖሊሲ በሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የግብርና ኤክስቴንሽንን ምንነት፣ አላማና ተግባራት በትክክል መወሰን ይኖርበታል።

- ግብርናን በተመለከተ መንግስት ተለዋዋጭ የትኩረት አቅጣጫ ፍንጮች በመስጠቱ የተነሳ የግብርና ኤክስቴንሽን የሚሰሩ ሠራተኞች በተወሰኑ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው ረዘም ላላ ጊዜ እንዳይሠሩ ምክንያት እየሆነ መጥቷል። ለምሳሌ ከምግብ እህል ወደ ገበያ ሰብሎች፣ ከዚያም ወደ ውሃ ማሰባሰብ ወዘተ የተቀያየሩ ትኩረቶች ነበሩ። ይህም ቀደም ሲል ታቅደው በተሰሩ ስራዎች በሚገባ ስለማይጠናቀቁ ከነሱ ሊገኙ የሚችሉ ተሞክሮዎችን ለመዳሰስና ለመማር እንዳይቻል ያደርጋል።
- ያልተማከለ አስተዳደርና ከማስፈንና ቅንጅትን ከመፍጠር አኳያ የሚታዩ ክፍተቶችን መዝጋት ያሻል። የሀገሪቱ ህገ መንግስት ያልተማከለ አስተ ዳደርን በማበረታት ለወረዳዎች ሥልጣንን የሰጠ በመሆኑ ለአካባቢው ተስማሚ የሆነ የኤክስቴንሽን ሥራ አቅደው እንዲሰሩ ይጠበቃል። ይህ አሰራር ተገቢውን የካፒታልና የሰው ኃይል በወረዳ ደረጃ በማቅረብ አቅም መገንባትን ይጠይቃል፤ በወረዳ ደረጃም አስፈላጊውን የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት ይገባል።

**ማጠቃለያ**

በሶስቱም ስርዓቶች ኤክስቴንሽን አጠቃላይ አካሄድ በወቅቱ ፖለቲካዊ እምነት ላይ የተመሠረተና በአለም አቀፍ ደረጃ ዕርዳታ ሰጪዎች ያምኑበት በነበረው አካሄድ መሠረትም ሲቀያየር ቆይቷል። ለምሳሌ በ1950ዎቹ የማህበረሰብ ልማት፣ በ1960ዎቹ የተቀናጀ ፓኬጅ፣ በ1980ዎቹ የስልጠናና ጉብኝት ኤክስቴንሽን፣ ከ1990ዎቹ ወዲህ ደግሞ በምግብ ራስን መቻልና ዘላቂ ልማት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

የሀገሪቱ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች የቀልጣፋ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑ ከተፈለገ የኤክስቴንሽን ሥርዓቱ ያለበትን ቴክኒካዊ ችግሮች ማቃለልና በጥናት ላይ የተመሠረተ የኤክስቴንሽን ፖሊሲ በመቅረጽ ፖሊሲ ነክ የሆኑና ትኩረትን የሚሹ ቴክኒካዊ ጉዳዮችንም መዳሰስ ያስፈልጋል።

በሀገራችን ከአንድ የኤክስቴንሽን አካሄድ ወደ ሌለው ሲገባ ብዙውን ጊዜ አካሄዱን በሶስተኛ ወገን በመገምገም ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በእርዳታ ሰጪዎች ጫና እንደሆነ ይገመታል። በተጨማሪም የግብርና ሚ/ር አደረጃጀት በየጊዜው ተቀያይሯል። ይህም የሠራተኞችና የመዋቅር አለመረጋጋት እያመጣ ነው የኤክስቴንሽን ግልጋሎት ሽፋን በእጅጉ የጨመረ ቢሆንም አሁንም ማቀዱና መፈፀሙ አሳታፊ ነው ለማለት አይቻልም። የኤ ክስቴንሽን ትኩረትም በሰብል ብቻ ላይ ሆኗል። የእንስሳት፣ የደን፣ ግብይትና የእርሻ መሣሪያዎች ንዑስ ዘርፎች ብዙም አልተተኮረባቸውም። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በድርቅ በተደጋጋሚ የሚጠቁ ሀገሮች ብቃት ያለው የኤክስቴንሽን ሥርዓት በመዘርጋት የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ፣ ገበሬ ተኮር መሆን፣ እንዲሁም የገበሬዎችን ችግር በማጥናትና በመፍታት ላይ የሚሰራ ምርትና ምርታማነት መጨመርና ተጨማሪ እሴት መፍጠር ላይ ማተኮር አለበት።

ለማጠቃለል ይህ ሪፖርት ስለኤክስቴንሽን አጠቃላይ ግንዛቤ ሰጥቶ የኢትዮጵያን የግብርና ኤክስቴንሽን ታሪካዊ ሂደትና ወቅታዊ ሁኔታ በመመርመር ተጓዳኝ ፖሊሲ ዎችን በመቃኘት የኤክስቴንሽን ግልጋሎቱ ይበልጥ የተ ሳካ ለማድረግ መፍትሄ የሚሹ ቴክኒካዊና ፖሊሲ-ነክ ችግሮችን ይቃኛል። የግብርና ኤክስቴንሽን ይበልጥ የተ ሳካ የሚሆነው የኤክስቴሽን ፖሊሲ ወጥቶለት አካሄዱ፣ ስፋቱ ትኩረቱንና ተግባራቱ በትክክል ሲቀመጥለትና በሥርዓቱ ውስጥ ተዋናይ የሆኑት አካላት (የመንግስት ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ) ሚናም ተገልጾ ተደጋጋፊነታቸውም ሲረጋገጥ ነው። በመጨረሻም የኤክስቴንሽንን ዓላማና ተግባር በተ ሻለ መልኩ የሚገልጽ፤ በዚህ መስክ የተሰማሩ ተቋማትም ይበልጥ አገልግሎታቸውን የተደጋገፈና የተናበበ ማድረግ የሚያስችል፤ ሀገራዊ ፕሮግራሞችም እንዴት እንደሚታቀዱ፣ እንደሚተገበሩ እና እንደሚገመገሙ የሚያብራራ ራሱን የቻለ የኤክስቴንሽን ፖሊሲ ሀገሪቱ እንደሚያስፈልጋት ይጠቁማል።

**(ሀብተማርያም ካሣ)**

**ምንጭ፡-** ታዬ አሰፋ (አርታኢ)፣ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሐግብሮች ጥንቅር»፣ ገፅ 157-178፣ አዲስ አበባ፣ ማጥመ፣ 2001 ዓ/ም።


<u>ምስጋናና ማሳሰቢያ</u>

ይህ ሰነድ የታተመው በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው። ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የአውሮፓን ሕብረት አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም።



<u>አድራሻ</u>: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-629 78 88/91♦ ፋክስ: 011-629 78 89
ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et